ከጎረቤትዎ ቤት ሆነው፣ በሞባይል ስልክ ወይም የህዝብ ስልክ በመጠቀም ለፖሊስ ይደውሉ።

» በማታ  አንድ ሰው ቤትዎን ሲሰብር የሰሙ ከመሰለዎት፣ ከቻሉ ቀስ ብለው ይውጡ እና ለፖሊስ ይደውሉ። መውጣት ካልቻሉ ስልክ ያለበት ክፍል ውስጥ በሩን ቆልፈው ለፖሊስ ይደውሉ። ሌባው ክፍልዎ ውስጥ ከሆነ እንደተኙ ያስመስሉ።
» አንድ በጣም ጠቃሚ ማስታወሻ--ቤትዎ አለመሆንዎን ወይም ብቻዎን እንደሚኖሩ ፍንጭ የሚሰጥ መልዕክት በስልክ መመለሻዎ ላይ አይተው። “ለጊዜው አንገኝም” የሚል መልዕክት ያስቀምጡ። ብቻዎን መንዳት ያቁሙ።  በተለይ በማታ ከአንድ ሰው ጋር ይሂዱ።

## ንብረትዎን ይወቁ

ከላይ የተጠቀሱትን ማድረግ በሌቦች መጎዳትን ሊቀንሱ ቢችሉም እቤትዎ ወስጥ ያለውን ነገር በማወቅ የበለጠ ጉዳትን እና ውጣ ውረድን ማስወገድ ይችላሉ።  ከቀላሎቹ አንደኛው መንገድ የዕቃዎችዎን ዝርዝር መያዝ ነው-- ዋጋ ያላቸውን እንደ ሰዓቶች፣ ጌጦች፣ የኤሌትሪክ መሣሪያዎች፣ የኃይል መሣሪያዎች እና የወጥ ቤት መሣሪያዎችን በሙሉ በጽሁፍ ያስቀምጡ።

በተጨማሪም “ኦፕሬሽን አይዲ” በተባለው ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎቾ እንዴት አድርገው ምልክት እንደሚያደርጉ የሚረዳ ነጻ ፕሮግራም መካፈል ይፈልጉ ይሆናል።  የበለጠ ለማወቅ በድህረ ገጽ www.mpdc.dc.gov/operationid ይመልከቱ።  ዋጋ ያላቸው ዕቃዎችዎን የመሸጥ እድላቸውን ለመቀነስ ከድህረ ገጹ ላይ የማስጠንቀቂያ ፖስተር በመገልበጥ ሊሰርቁ ለሚመጡ ሌቦች ማስጠንቀቂያ መስጠት ይችላሉ። በተጨማሪም የንብረት ዝርዝር መጻፊያ ቅጽ ግልባጭ በመውሰድ ምን ላይ ምልክት እንደሚያደርጉ መማር ይችላሉ።

OPERATION ID
WASHINGTON, DC

**የበለጠ የደህንነት ፍንጮች ያግኙ**

በቀን ተቀን ህይዎትዎ በሌሎች መንገዶች ከወንጀል ለመከላከል በድህረ ገጻችን ላይ የሚገኙ ሌሎች መጽሄቶችን በ**www.mpdc.dc.gov/safety** ይመልከቱ። ወይም ከአካባቢው የፖሊስ ዲስትሪክ ይጠይቁ። በአቅራቢያዎ ያለውን ለማወቅ **www.mpdc.dc.gov/districts**ን ይጎብኙ።

## ይሳተፉ

ማንኛውም ግለሰብ ወይም ኤጀንሲ ወንጀልን ብቻውን ሊያቆም አይችልም።  ፖሊስ እና ዜጎች በአንድነት መሥራት አለባቸው። የኮሎምብያ ዲስትሪክት ህብረተሰብ የፖሊስ ጥበቃ ዘዴ ፖሊስ እና ህብረተሰቦች ወንጀልን ለመከላከል እና ጉዳት የሌለባቸው አካባቢዎች ለመገንባት የሚያስችሉ በአንድነት የሚያሠሩ ብዙ መንገዶች ይሰጣል። ይህም የፖሊስ አገልግሎት አካባቢ ስብሰባዎችን፣ የዜጎች ተጠባባቂዎች እና ሌሎችንም ያጠቃልላል።  በአካባቢዎ ስላሉ የህብረተሰብ ጥበቃ እንቅስቃሴዎች ለማወቅ ለአካባቢዎ የፖሊስ ዲስትሪክት ይደውሉ፣

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1ኛ ዲስትሪክት | ዋና:...... | (202) 698-0555 | .........TTY: | 727-8506 |
| | ቅርንጫፍ:...... | (202) 698-0068 | .........TTY: | 543-2352 |
| 2ኛ ዲስትሪክት | ዋና:...... | (202) 715-7300 | .........TTY: | 364-3961 |
| 3ኛ ዲስትሪክት | ዋና:...... | (202) 673-6815 | .........TTY: | 518-0008 |
| 4ኛ ዲስትሪክት | ዋና:...... | (202) 715-7400 | .........TTY: | 722-1791 |
| | ቅርንጫፍ:...... | (202) 576-8222 | .........TTY: | 576-9640 |
| 5ኛ ዲስትሪክት | ዋና:...... | (202) 698-0150 | .........TTY: | 727-5437 |
| 6ኛ ዲስትሪክት | ዋና:...... | (202) 698-0880 | .........TTY: | 398-5397 |
| | ቅርንጫፍ:...... | (202) 698-2088 | .........TTY: | 281-3945 |
| 7ኛ ዲስትሪክት | ዋና:...... | (202) 698-1500 | .........TTY: | 889-3574 |

## ስለወንጀል የሚያውቁት ነገር አለ? በሚስጥር አይያዙት።

ለፖሊስ መንገር የሚፈልጉት ጠቃሚ መረጃ ካለዎት፣ ስም የማይገልጽ የወንጀል ፍንጭ መስጫ መስመር እና የቴክስት ፍንጭ መስመር ለሜትሮፖሊታን ፖሊስ ጠቃሚ መረጃ ማንነትዎን ሳይገልጹ እንዲሰጡ ይረዳዎታል። በስልክ ቁጥር **(202) 727-9099** ወይም በቴክስት 50411 24 ሰዓቶች በቀን፣ ስባት ቀኖች በሳምንት።  ስምዎ ሳይጠቀስ መረጃው በቻ ይወሰዳል።  መረጃዎ የገንዘብ ሽልማት ሊያስገኝ ይችላል።  ለበለጠ ዝርዝር በድህረ ገጽ **www.mpdc.dc.gov/tipline** ይመልከቱ።

GIVE 5-0 THE 4-1-1

ለፖሊስ መረጃ አለዎት?
**(202) 727-9099 ይደውሉ**
**50411 ቴክስት ያድርጉ**

Government of the District of Columbia
Metropolitan Police Department
300 Indiana Avenue, NW
Washington, DC 20001

*June 2013*

# ለደህንነትዎ



# ስርቆትን መከላከል

ከስርቆት፣ በኃይል መግባት እና ቤትዎን ከመወረር ለመጠበቅ የሚረዱ ፍንጮች

# ቤትዎን ኢላማ አያድርጉ.

**ቤትዎ ተቆልፎብዎት ያውቃል? ያም ሆነ ይህ መግባት ችለው ነበር? የራስዎን ቤት መስበር ከቻሉ ሌላም ሰው የእርስዎን ቤት ለመስበር የዚያኑ ያህል ቀላል ነው። ቤት ሰብሮ ለመግባት የሚሞክሩ በዙ ሌቦች ከ60 ሰኮንድ በላይ አይፈጅባቸውም።.**

ወደፊት ለሚሆን ስርቆት መተንበያ ያለፈ ስርቆት ነው። ስለዚህ፣ የመከላከያ እርምጃ አሁን መውሰዱ ጠቃሚ ነው። ጠንካራ መቆለፊያዎች - እና አንዱ ለአንዱ የሚጠባበቁ ጥሩ ጎረቤቶች - ለስርቆቶች ጠቃሚ መከላከያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የሚከተሉት ጥቂት ፍንጮች እራስዎን እና ንብረትዎን የማይጎዳ እና የተጠበቀ ለማድረግ ይረዳሉ።

## የበር ቁልፎችዎን ይመርምሩ

» እያንዳንዱ የውጭ በር ጠንካራ እና በደንብ የተገጠመ ቁልፍ እንዲኖረው ያረጋግጡ። በበሩ መክፈቻ ላይ ያሉ ቁልፎች ብቻ በቂ አይደሉም።

» ተላላፊ የመስተዋት በሮች በደንብ ካልተገጠሙ ሌባ በቀላሉ እንዲገባ ያስችላሉ። ከውስጥ መጥረጊያ ወይም ብረት በማስገባት ወይም ለንግድ የተዘጋጁ ቁልፎች በማስገባት በሩ እንዳይከፈት ማድረግ ይችላሉ። በሩ ከመተላለፊያው ላይ እንዳይወልቅ በተላላፊው በር ፍሬሞች እና በቋሚው ፍሬም በኩል ቀዳዳ ይፍጠሩ። ቀጥሎም ምስማር ቀዳዳው ውስጥ ያስገቡ።

» ሁለት ተላላፊ መቆለፊያ ያላቸው መስኮቶችን በቁልፍ ወይም በውጭ እና በውስጥ ፍሬሞች መካከል ትንሽ ቀዳዳ በ45 ዲግሪ ማእዘን በመብሳት ሊወገድ የሚችል ምስማር አስገብተው ይቆልፏቸው። የምድር ቤት መስኮቶችን ማስገባት በማያስችል መከላከያ (እሳት ከተነሳ ከውስጥ መከፍት የሚቻል መሆኑን አረጋግጠው) ይግጠሙዋቸው።

» ቁልፎችን ምን ጊዜም ከቤትዎ ውጭ አይደብቁ! ባይሆን ለሚያምኑት ጎረቤት ትርፍ ቁልፍ ይስጡ።

» አዲስ ቤት ወይም አፓርትመንት ሲገቡ ቁልፉን ይለውጡ።

## በሮችዎን ይመርምሩ

አንዴ በራችንን ከዘጋን እና ከቆለፍን ጉዳት የማይደርስብን እና የተጠበቅን ይመስለናል፣ እውነቱ ግን ጠንካራ ያልሆነ በር ላይ ያለ ቁልፍ ልክ የመኪና በርዎን ቆልፈው መስተዋቱን ሳይዘጉ የገንዝብ ቦርሳዎን የፊት ወንበር ላይ እንደ ማስቀመጥ ነው!

ቤትዎን የተቻለውን ያህል አስጊ እንዳይሆን የሚከተሉትን እርምጃዎች ይውሰዱ።

» ሁሉም የውጭ በሮች የብረት ወይም ጠንካራ እንጨት መሆን አለባቸው።

» በሩን ሳይከፍቱ ውጭ ያለው ሰው ማን እንደሆነ ለማየት ቀዳዳ ወይም ሰፊ የማያ ቀዳዳ በሁሉም የመግቢያ በሮች ላይ ያስገቡ። የበር ሰንሰለቶች በቀላሉ ስለሚሰበሩ ሌቦችን አይከላከሉም።

» በሮችዎ በፍሬማቸው ላይ በደንብ የማይገጥሙ ከሆነ የአየር መከላከያ ዙሪያውን ያስገቡበት።



## ውጬን ይመርምሩ።

ቤትዎን ከውጭ ይመልከቱ እና የተቻለውን ያህል አስጊ እንዳይሆን የሚከተሉትን ፍንጮች ይከተሉ፣

» ሌቦች ብሩህ የሆነ መብራት አይወዱም። የውጭ መብራቶች ያስገቡ እና ሌሊቱን ሙሉ ያብሯቸው። በተለይ በእንቅስቃሴ የሚበሩ መብራቶች ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ።

» ሜዳዎን ንጹህ ያድርጉ፡፡ በርካታ ግንድ ያላቸው ተክሎች በሮችን ወይም መስኮቶችን እንዳይከልሉ ይመልምሏቸው። ወደላይ ያለ መስኮት ላይ ለመውጣት የሚረዱ የዛፍ ቅርንጫፎችን ይቁረጡዋቸው።

» በጉዞ ላይ ከሆኑ በየሰዓቱ የሚበሩና እና የሚጠፉ መብራቶች (ምናልባትም ቴሌቪዥን ወይም ሬድዮ) ቀኑን በሙሉ እና ሌሊት በቤትዎ በተለያዩ ቦታዎች ያድርጉ። ለ24 ሰዓቶች የሚበሩ መብራቶች ባዶ ቤት መሆኑን ያመለክታሉ!

» ጥላ ማጥሊያዎችን፣ ስክሪኖችን እና መጋረጃዎችን በተለመደ ቦታዎች ይተው።

» ፖስታዎችዎ እና ጋዜጣዎችዎ እንዳይጠራቀሙ ያረጋግጡ! ፖስታ ቤቱን እና ጋዜጣ ላኪዎችን ማምጣት እንዲያቆሙ ይደውሉላቸው ወይም ጎረቤት እንዲያነሳልዎት ይጠይቁ።

» ቁሻሻዎን ወይም እንደገና የመጠቀሚያ ማጠራቀሚያዎችን ከመንገድ ዳር አስቀምጠዋቸው ከሆነ ከተማውን ለቀው ከመሄድዎ በፊት ወደ ጓሮ ይመልሱ ወይም ጎረቤትዎ እንዲመልስልዎት ይጠይቁ።

## ውስጡን ይከላከሉ

» ጠቃሚ ዕቃዎችን እንደ ቪሲአር፣ ዲቪዲ፣ ስቴርዮ፣ ኮምፒውተሮችን እና ጌጦችን ዝርዝር በጽሁፍ ይያዙ። ፎቶግራፍ ያንሷቸው እና የመለያ ቁጥራቸውን እና ገለጻቸውን ዝርዝር ያስቀምጡ። ቤትዎ ከተሰረቀ ይህ መረጃ ለፖሊስ ይረዳል። ለተጨማሪ ጠቃሚ መረጃዎች “ዕቃዎችዎን ይወቁ” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

» ለነጻ የቤት ጥበቃ ጥናት የዲስትሪክትዎን ፖሊስ ያነጋግሩ።

## ሌቦች ከመስረቅ በላይ የበለጠ ሊያደርጉ ይችላሉ።

አብዛኛዎቹ ሌቦች ሰው በሌለበት ጊዜ መግባት ይመርጣሉ። ሰው የሌለበት ቤት ወይም ስው ቤቱ ውስጥ ካጋጠማቸው ሌቦች ሌሎች ወንጀሎችን እንደ መድፈር፣ ሰርቆት እና ድብደባ ሊፈጽሙ ይችላሉ።

» አንድ ነገር አጠራጣሪ ከመሰለዎት-- ክፍተት ያለው ስክሪን፣ የተሰበረ መስኮት ወይም በር-- ወደ ውስጥ አይግቡ!